# የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት

## THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA

HIS IMPERIAL HIGHNESS PRINCE ERMIAS SAHLE-SELASSIE HAILE-SELASSIE
PRESIDENT

ጥር ፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓም ልዑል ኤርምያስ ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ፥ የኢትዮጵያ ዘውድ ምክር ቤት ፕሬዚደንት እና የኢትዮጵያ ንጉሣዊ በጎ አድራጎት ባለአደራ ድርጅት የበላይ ጠባቂ፥ ከባለቤታቸው ከልዕልት ሳባ ከበደ እና ሌሎች የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት ጋር ሆነው የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት ተፈጽሞ የካቴድራሉ ምርቃት ላይ ተገኝተዋል። እንደሚታወሰው ልዑል ኤርምያስ ለካቴድራሉ የእድሳት ኮሚቴ መዋጮ አምባሳደር እንዲሆኑ በካቴድራሉ እድሳት እና ልማት ኮሚቴ ተወስኖ ከአገር ውጭ ሲያሰባስቡ ቆይተዋል።

የካቴድራሉ ታቦታት በክብር ከበዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያን ወተው በካቴድራሉ አውደ ምህረት ከደረሱ በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ፥ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ፥ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም፥ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሐይማኖት ከብፁዐን አበው ሊቃነ ጳጳሳት እና በርካታ ካህናትና ዲያቆናት ጋር በመሆን ካቴድራሉን ውጪውንም ውስጡንም ባርከው መንበሮቹንም እንደዚሁ ከባረኩ በኋላ ታቦታቱ ወደ መንበረ ክብራቸው ተመልሰዋል። ልዑል ኤርምያስ፥ ልዕልት ሳባ እና ሌሎቹም የንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት የክብር እንግዶች ሆነው ግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ያሰሩትን ይዚህን ታላቅ ካቴድራል ምረቃት ላይ ተገኝተው ተሳትፈው ከበዓሉ በረከት ተካፍለዋል። የካቴድራሉ አመራሮችና የእድሳትና ልማት ኮሚቴ ለልዑል ኤርምያስ በእድሳት መዋጮ ያደረጉትን በማንሳት ለልዑልነታቸው ልዩ ምስጋና አበርክተዋል።

ቅዱስ ፓትርያርኩ ለዚህ ታላቅ ቀን ባስተላለፉት መልእክት እንዳሉት በሙሴ ዘመን ጥንት እስራኤላዊይን

*"…የመግናኛው ወይንም የማደርያው ድንኳን ተብሎ ይጠራ የነበረው ደብተራ ኦሪት በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ መሠረት ተሰርቶ ክነአግልጋዮቹ በቡራኬ ከብሯል። (ዘጸ 30.22) ከደብተራ ኦሪትም ቀጥሎ በእየሩሳሌም ከተማ በልዩ ጥበብ የታነፀው የሰሎሞን ቤተ ምቅደስም በታላቅ ሥነ ሥርዓት በልዑል እግዚአብሔር ስም ተቀድሶ ለ364 ዓመታት ያህል አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ የነበሩት ደብተራ ኦሪት እና መቅደሰ ሰሎሞን ካለፉ በኋላ "ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ" ይሚለው የትንቢት ቃል የይፈጸም ዘንድ በደመ ውልድ እግዚአብሔር ተመሥርታ "ጸርሐ ጽዮን" በሚባለው ስያሜ በቅዱስ ማርቆስ እናት ቤት አገልግሎቷን የጀመረችው የመጀመሪያዋ የሐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ስብከት እና በሊቃውንት ትምህርት ተስፋፍታ ከእኛ ዘመን ደርሳለች። . . .ስለ ሆነም በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥትነት ዘመን በአስደናቂ ጥበብ የተገነባው የቤተ ክርስቲያናችን ታላላቅ በዓላት የሚከበሩበት፤ የአርእስተ አበው ቅዱሳን ፓትርያርኮች እና የብፁዓን ኤጲስ ቆጶሳት ሢመት የሚፈጸምበት፤ የሀገር መሪዎች እና ታላላቅ ሰዎች ዐረፍተ ዘመን ሲገታቸው በልዩ ሥነ ሥርዓት የሚሸኙበት፤ እንዱሁም ዐፅማቸው በክብር የሚያርፍበት የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ረጅም ጊዜን በማስቆጠሩ የደረሰበት እርግና አሳስቧችሁ የእድሳት ሥራውን ለማከናወን ስትፋጠኑ የነበራችሁ ከካቴድራሉ ሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ጽ/ቤት ጀምሮ በየደረጃው ባለው የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የምትገኙ፤ ከሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ሆናችሁ ለዕድሳት ሥራው የአቅማችሁን ድጋፍ ያደረጋችሁ የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻችን ያበረከታችሁት አስተዋጽኦ በታሪክ መዝገብ በደማቁ የሚሠፍር ሆኖ ዛሬ የድካማችሁን ፍሬ ለማየት በመብቃታችሁ ስለ እናንት እግዚአብሔርን እያመሰገንን እንኳን ለዚህ ታላቅ በዓል በሰላም እደረሳችሁ! እንኳን ደስ አላችሁ! ለማለት እንወዳለን።"*

ልዑል ኤርምያስ ይህ በአያታቸው የታነጸው እና የሳቸውና የታላቅ አርበኞች መታሰብያቸው የሆነው ታላቅ ቤተ መቅደስ በመታደሱ የተሰማቸውን ታላቅ ደስታ ግልጸዋል። ለተበረከተላቸውም ምስጋና የተሰማቸውን ክብር ገልጸዋል።